## *የጸረ ጭቆናው ኣመጽ እስከ ኦሮምያ ነጻነት ድረስ ተጠናክሮ ይቀጥላል*

*(የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ)*

ሀዳር 9 ቀን 2005 በኦሮሞ ነጻነት ግንባር በታወጀው መሰረት በመላው ኦሮምያ የጸረ ጭቆና ኣመጽ ይበልጥ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የቀጠለበት ታሪካዊ እለት ነው። ዛሬ ህዳር 2012 ላይ ቆመን ኣመጹ የታወጀበትን 7ኛ ኣመት እንዘክራለን።

ይህ የጸረ ጭቆና ኣመጽ በዚህ እለት (ህዳር 9 ቀን 2005) ለምን በተቀናጀ መልኩ ታወጀ? ያኔ ምን ኣይነት ሁኔታዎች ነበሩ፣ ዛሬስ ምን ውስጥ እንገኛለን? ወደፊትስ ምን ይበጃል? እነዚህን ጥያቄዎች በኣጭሩ መመለስ ኣስፈላጊ ይሆናል። በርግጥ የኦሮሞ ህዝብ በጠላቱ ላይ ማመጽ የጀመረው በጠመንጃ ሃይል ተበልጦ ከተንበረከከበት ወቅት ኣንስቶ ነበር። ከዚያ ወቅት ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ ህዝባችን በሚገኝባቸው ኣካባቢዎች ሁሉ በተለያዩ ስልቶች ለነጻነቱ ከመታገል ወደ ሁዋላ ያለበት ጊዜ የለም።

በኣዲስ መልክ የተቀናጀው የጸረ ጭቆና ኣመጽ ህዳር 9, 2005 በታወጀበት ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ስቦ የነበረው ጉዳይ በወቅቱ ተካሄዶ ስለነበረው ምርጫ ውጤት ነበር። በዚያ ምርጫ ላይ የኦሮሞ ህዝብ ድምጽ የታፈነ ስለመሆኑ የሚዘነጋ ኣይደለም። ይበልጥ ገኖ ይሰማ የነበረው የፖለቲካ ድምጽ በምርጫው ላይ በስፋት የተሳተፉት ገዢው ፓርቲና የቅንጅት ፓርቲ ድምጽ ብቻ ነበር። በምርጫው ውጤት መሰረት በነዚህ ሁለቱ ፓርቲዎች መካከል የተነሳው ውዝግብ ለኣስርት ኣመታት ሲካሄድ በኖረው ኣንጋፋው የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ድምጽ ላይ ጥላውን ኣጠላበት። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ጥያቄ በምርጫው ላይ የተሳተፉት የሁለቱ ሃይሎች ጥያቄ ብቻ መስሎ እንዲታይ ኣደረገው። ለዘመናት የዘለቀው የተጨቁዋኝ ህዝቦች የትግል ድምጸና ብሶት ታፈነ።

ይህ ሁኔታ በዚያው መልኩ ቢቀጥል ኖሮ በኦሮሞ ህዝብ ትግል ሂደት ላይ የሚደቅነው ኣደጋ ቀላል ኣይሆንም ነበር። ኣደጋውን ለማስቀረት ሲባል የታፈነውን የኦሮሞና የሌሎች ተጨቁዋኝ ህዝቦችን ድምፅ ዳግም በተቀናጀ መልኩ ማሰማት የግድ ሆነ። በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ከገዢው መንግስትም ሆነ በተቃዋሚነት ከተሰለፉት የቀድሞው ስርኣት ኣቀንቃኞች የተለየና በራሱ ጥያቄዎች ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ለኣለም ማህበረሰብ ማስገንዘብ ጊዜ የማይሰጠው ኣንገብጋቢ ጉዳይ ሆነ። ከዚህም በመነሳት ነበር ኦነግ ህዳር 9 ቀን 2005 በይበልጥ በተቀናጀ መልኩ በመላው ኦሮምያ የጸረ ጭቆና ኣመጹ እንዲቀጣጠል ያወጀው።

የኣመጹ ኣዋጅ በወቅቱ ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱ የምርጫው ተሳታፊ ሃይሎች መካከል ገኖ በሚሰማው ድምፅ ታፍኖ የቆየውን የኦሮሞ ህዝብ ድምጽ እንደገና ነፍስ ዘራበት። የተሰበረውን የኦሮሞ ህዝብ ቅስም መልሶ ጠገነው። ኦሮሞ በራሱ ጥያቄ ላይ የተመሰረተ የራሱ የሆነ ኣንገብጋቢ ጥያቄ ያለው መሆኑን በተቀናጀ መልኩ እንዲያሰማ መራው። የወያኔ መንግስት የኣመጹን ሂደት ዜና ለማፈን በተቻለው መጠን ጥረት ቢያደርግም በርካታ የኣለም መገናኛ ብዙሃን ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው የዘገባ ሽፋን ሲሰጡት ቆይተዋል። የወቅቱ የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ሃገር ውስጥ የጸረ ጭቆና ኣመጹ ገኖ እንዳይሰማ ለማፈን ቢሞክርም ከኣሜሪካ መንግስት

ጋር በጉዳዩ ላይ በጽኑ ሲመክር ነበር። በኦሮምያ ውስጥ በፈነዳው የህዝብ ኣልገዛም ባይነት ኣመጽ በእጅጉ የተደናገጠው የወያኔ መሪ ድጋፍና ምክር ፍለጋ ሸገር ውስጥ በሚገኘው ኤምባሲ ኣማካኝነት ለኣሜሪካ መንግስት ማመልከቱን ከጥቂት ወራት በፊት ዊኪሊክስ ማጋለጡ ኣይዘነጋም። በሰፊው የኦሮምያ ኣካባቢዎች ሁሉ በኣንድ ተመሳሳይ ቀን ፈንድቶ የተቀጣጠለው ጸረ ጭቆና ኣመጹ የኦሮሞ ህዝብ ምንም ያህል በጂኦግራፊ ያዊ ኣሰፋፈር ቢራራቅም ፍላጎቱ ግን ኣንድና ተመሳሳይ መሆኑን ለጠላትም ለወዳጅም ኣረጋገጠ። ኣመጹ ሰላማዊ ሰልፎች በመውጣት ሰው በላውን ስርኣት ማውገዝ፣ ትምህርትና ስራ ማቆም፣ የገበያ ኣድማና ሌሎችም ተዛማጅ ስልቶችን ያቀፈ ነበር።

በጸረ ጭቆና ኣመጹ በርካታ ውድ መስዋእትነቶች ተከፍለዋል ኣስከ ዛሬም እየተከፈሉ ናቸው። በተለይም የኦሮሞ ወጣቶች ለሰፊው ህዝባቸው ኣርኣያ በመሆን ነጻነት የምትጠይቀውን ዋጋ ሲከፍሉ ኖረዋል ዛሬም እንዲሁ። በእለቱ በተቀናጀ መልኩ የተለኮሰው የኣመጽ ችቦ እስከዛሬም ድረስ እንደ ሰደድ እሳት በመቀጣጠል ጠላቶችን ሲፈጅ ለወዳጅ ደግሞ የማይጠፋ የተስፋ ብርሃን እየፈነጠቀ ይገኛል። በዚህ ታሪካዊ ኣመጽ በተለያዩ የኦሮምያ ቀበሌዎች የተሰዉ፣ ለኣካል ጉድለት የተዳረጉ፣ በእስር የተንገላቱና ሃብት ንብረታቸውን የተዘረፉ ታጋዮች ሁሉ ዘላለም ይዘከራሉ።

ዛሬ የኣመጹን መቀጣጠል 7ኛ ኣመት ስንዘክር ምን ኣይነት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን ብሎ መጠያየቁ ኣስፈላጊ ይሆናል። ኣዎን፣ ዛሬ ለነጻነት የሚደረገውን ዘርፈ ብዙ ትግል ይበልጥ ለማፋፋም የሚያስገድዱን ሁኔታዎች ውስጥ እንገኛለን። በህዝባችን ላይ የሚካሄደው ኣፈናና ዘረፋ በባሰ መልኩ ከፋ እንጂ መሻሻልን ኣላሳየም። የኦሮሞ ህዝብ ዛሬ ስልጣን ላይ ባለው መንግስት ብቻ ሳይሆን ወደ ስልጣን ለመውጣት በሚያልመው በቀድሞው ስርኣት ናፋቂ ሃይል ዘንድም በክፉ ኣይን የሚታይ ህዝብ መሆኑ በገሃድ እየተስተዋለ ነው። ህዝባችን በትግሉ እስካሁን ያረጋገጣቸው የማይናቁ ድሎች ተቀልብሰው ቀና ማለት የጀመረው ኣንገቱ ዳግም እንዲደፋ በስውርም በገሃድም የሚሸረቡ ሴራዎች ሁሉ ቀላል ኣለመሆናቸውን በጥንቃቄ እየገመገምን ነው። ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የኦሮሞን ህዝብ እንደ ደመኛ ጠላቱ በመፈረጅ በተቻለለት መንገድ ሁሉ ሲዘምትበት እናያለን። ሌላው ቀርቶ የስርኣቱ ኣካል ናቸው የሚባሉት የኦፒዲኦ ኣባላት ሳይቀሩ ኦሮሞ በመሆናቸው ብቻ ይናቃሉ። በመንግስቱ ውስጥ ብዙሃንን ህዝብ እንደመወከላቸው መጠን የሚመጥናቸውን ትርጉም ያለው ስልጣን እንዳይዙ ታግደዋል። በህገ መንግስቱ ውስጥ ያላቸውን መብቶች እንዳይጠቀሙም ተገፍተዋል።

ከዚሁ ጎን ለጎን በሃይማኖት ሽፋን በህዝባችን ላይ ኣነጣጥሮ እየተካሄደ የሚገኘውን ኣምባገነናዊ ዘመቻ ማንሳት የግድ ይሆናል። የወያኔ መንግስት ለሃይማኖቱ ነጻነት የሚታገለውን ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሌላ ታፔላ እየለጠፈበት እየመታው ይገኛል። የጥቃቱ ኢላማ በእስልምና ሃይማኖት ላይ ብቻ ያነጣጠረ ሳይሆን በይበልጥ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ የኦሮሞ ተወላጆችን ለመምታት ያቀደ መሆኑ በገሃድ እየታየ ነው። እስካሁን በዚህ ጸረ ሃይማኖት ጥቃት ዘመቻ እየተመቱ ያሉት የኦሮሞ ተወላጆች ናቸው። በኣርሲ ገደብ ኣሳሳ፣ በፊንፊኔ፣ በወሎ ገርባ፣ ከሚሴና በሌሎችም የኦሮምያ ኣካባቢዎች የተወሰዱት ዘግናኝ የግድያ፣ የድብደባና የእስራት እርምጃዎች ለዚህ እውነታ ምስክር ናቸው። የሙስሊሙ ማህበረሰብ መገኛ ኦሮምያ ውስጥ ብቻ ይመስል በሙስሊሙ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ኦሮምያ ላይ ብቻ መወሰኑ ለኦሮሞ ህዝብ

የሚያስተላልፈው ራሱን የቻለ መልእክት አለው። እንዲህ ማለታችን ግን ከኦሮምያ ውጪም የሚገኘው የሙስሊሙ ደህንነት ኣያሳስበንም ከሚል ኣቁዋም ኣለመሆኑን ኣበክረን ማስገንዘብ እንወዳለን። ይህ መንግስት ኦሮሞውን ለመምታት ሲያሻው በኦነግ ደጋፊነት ሌላ ጊዜ ደግሞ በ"ሃይማኖት ኣክራሪነት" ስም ይመጣበታል።

ባጠቃላይ መልኩ ሲታይ ዛሬ የኦሮሞ ህዝብ የሚገኝበት ሁኔታ ኣመጽና ሌሎችንም የትግል ስልቶች በመጠቀም ኣምባገነናዊውን ግፍ ለማስቀረት መፋለም የሚጠይቅ ኣንገብጋቢ ወቅት መሆኑን ማስታወስ እንወዳለን። ህዳር 9 ቀን 2005 በተቀናጀ መልኩ የተቀጣጠለው የጸረ ጭቆና ኣመጽ ዛሬ ከ7 ኣመታት በሁዋላም በይበልጥ መሰረቱን ኣስፍቶ የመፋፋሙ ኣስፈላጊነት ካሉት ዋና ዋና የትግል ኣማራጮች ኣንዱ ይሆናል። በገፍ እየተረገጠ የሚገኘው የህዝባችን መብት የሚከበረው በልመናና በልምምጥ ሳይሆን እምቢ ለጠላት በማለት ኣይበገሬነትን በተግባር በማስመስከር ብቻ ይሆናል። ጀግኖች የኦሮሞ ታጋዮች ኦሮምያ ጠላት እጅ ከወደቀችበት ወቅት ኣንስቶ ሲከፍሉ የኖሩት ውድ መስዋእትነት ፍሬያማ የሚሆነው ዛሬ በህይወት ያለው ትውልድ ለጠላት ኣልበገር ብሎ ትግሉን ሲያፋፍም ብቻ ነው። የኦሮሞ ህዝብ ብዛትና የኦሮምያ ስፋት የሚመጥናቸውን ዋጋና ክብር የሚያገኙትም ሃይላችንን ኣስተባብረን ተደራጅተንና ተቀናጅተን ስንታገል ይሆናል። ስለሆነም የጸረ ጭቆናው ኣመጽ በተቀናጀ መልኩ የታወጀበትንና የተፋፋመበትን 7ኛ ኣመት ስንዘክር ይበልጥ ጠንካራ የሆነ የትግል ቁርጠኝነት ኣዳብረን ፍልሚያውን ለማፋፋም በመነሳት ይሆናል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

ህዳር 2012